የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ቁጥር OFAGF-04/24/S/9
ቀን 25/07/2015

ለክቡር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ
የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር
አዲስ አበበ፤

ጉዳዩ፡- የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርትን ይመለከታል፣

ከላይ በርዕሱ የተጠቀሰውን ኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 3 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 6 ገጽ የሂሣብ መግለጫዎች በድምሩ 9 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ገርማ በላቸው ታደሰ
የአገልግሎት ሰጪ መስሪያ ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

Office of the Federal Auditor General

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2015

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን
የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

ኮሚሽኑ የተመደበለትን በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ሥራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 እና በማሻሻያ ቁጥር 1146/2011 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፤ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ኮሚሽኑ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኮሚሽኑ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

- የገቢ /የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የ2014 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት፤ በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን ጠብቆ የተከናወነ በመሆኑ በእኛ አስተያየት በኮሚሽኑ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች እና የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓቱ አጥጋቢ ሆኖ ተገኝቷል።

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል።

1. <u>ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)</u>፤

3.1. የኮሚሽኑ ንብረት አስተዳደር በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት

አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

<u>በአላቂና ቋሚ ዕቃዎች ግምጃ ቤት፤</u>

- የዕቃዎች ገቢና ወጪ በቢን ካርድ ላይ ተሟልቶ ያልተመዘገበ መሆኑ፤
- ዕቃዎች በግምጃ ቤት ተደራርበው የተቀመጡ መሆኑ፤
- በመ/ቤቱ አዳራሽ ውስጥ ወጪ ያልተደረጉ ጠረጴዛዎች፣ የጨረታ ሳጥን እና የዕቃ መደርደሪያዎች የሚገኙ መሆኑ፤
- ሚኒ ኮንፍረንስ ጠረጴዛ ከቢሮ ውጭ ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑ፤
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የዕቃ ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ከንብረት መዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ያልተመሳከረ (ያልተመዛዘነ) መሆኑ፤ በኦዲቱ ውቅት ታውቋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

መጋቢት 2015

ጎርፋ በላቸው ታደሰ
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

የፌዴራል ዋና ኦዲተር
መ/ቤት

ቁጥር፡ OFAGF-04.24/5/8
ቀን 25/07/2015

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ለኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን

<u>አዲስ አበባ፤</u>

ጉዳዩ፡- <u>የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የ2014 በጀት ዓመት የመጨረሻ ሥራ አመራር ሪፖርትን ይመለከታል፣</u>

በርዕሱ የተጠቀሰውን የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦችን የያዘ 3 ገጽ የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት (Final Management Letter) ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡ በመሆኑም በገጽ 4 በተመለከተው የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች አተገባበር መርሃ-ግብር ቅጽ መሰረት የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ እንዲላክልን እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ገርማ በላቸው ታደሰ
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

Office of the Federal Auditor General

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን
የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ
የመጨረሻ ሥራ አመራር ሪፖርት

መጋቢት 2015

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

መግቢያ፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 እና በማሻሻያ ቁጥር 1146/2011 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት **የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን** የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የኮሚሽኑን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ፤

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የኮሚሽኑ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፤

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን ፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

ቀጥለው በተመለከቱት የኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲቱ **በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን** የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ **የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት** ኃላፊነት ነው።

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

1. <u>ንብረት፤</u>

1.1. <u>የንብረት አመዘጋገብ፤ አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ፤</u>

1.1.1. <u>ግኝት፤</u>

የኮሚሽኑ ንብረት አስተዳደር በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- የዕቃዎች ገቢና ወጪ በቢን ካርድ ላይ ተሟልቶ ያልተመዘገበ መሆኑ፤
- ዕቃዎች በግምጃ ቤት ተደራርበው የተቀመጡ መሆኑ፤
- በመ/ቤቱ አዳራሽ ውስጥ ወጪ ያልተደረጉ ጠረጴዛዎች፣ የጨረታ ሳጥን እና የዕቃ መደርደሪያዎች የሚገኙ መሆኑ፤
- ሚኒ ኮንፍረንስ ጠረጴዛ ከቢሮ ውጭ ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑ፤
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የዕቃ ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ከንብረት መዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ያልተመሳከረ (ያልተመዛዘነ) መሆኑ፤ በኦዲቱ ውቅት ታውቋል።

1.1.2. <u>ሥጋት፤</u>

- የዕቃዎች ገቢና ወጪ በአግባቡ ካልተመዘገበ የመንግስት ንብረትን በአግባቡ ለመቆጣጠር አያስችልም። እንዲሁም ለብልሹ አሰራር በር ይከፍታል።
- ዕቃዎች በግምጃ ቤት በአግባቡ ካልተቀመጡ ለብልሽት ሊዳረጉ ይችላሉ።
- የዕቃ ቆጠራ ከተደረገ በኂላ ቆጠራው ከንብረት መዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመሳከር (እንዲመዛዘን) ካልተደረገ የንብረት ጉደለት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ አያስችልም።

1.1.3. <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፧

በንብረት አመዘጋገብና አጠባበቅ ላይ የታዩ የአሰራር ክፍተቶች እንዲስተካከሉ የኮሚሽኑ ሥራ አመራር ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

1.1.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>፧

የኮሚሽኑ የዕቃ ግምጃ ቤት ጠባብ ሲሆን ችግሩን ለመፍታት ጥረት እያደረግን እንገኛለን፡፡ በንብረት አመዘጋገብ የታዩ ክፍተቶች እንዲስተካከሉ እናደርጋለን፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የስራ ትብብር እናመሰግናለን!

ግርማ ለቸው ታደሰ
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር